# የመኢአድ ላዕላይ ምክር ቤት አባላት
# እስራት እና መንገላታት
# እየደረሰባቸው መሆኑ ተገለጸ

አቶ ታዴዎስ ታንቱ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባል በደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና በወላይታ ሶዶ ዞን የማደራጀት ስራ ላይ እንዳሉ ጥቅምት 18/2001 ዓ.ም በሶዶ ዙሪያ ፖሊስ አዛዥ የፓርቲ ሰነዶችን መቀማታቸው ተገለጸ።

የአራዳ ፖሊስ አዛዥ መቶ አለቃ ጆቢር እና ባልደረቦቻቸው አቶ ታዲዎስ ታንቱ ባረፉበት የሶዶ ውበት ሆቴል ከለሊቱ 8.00 ሰአት የጥበቃ ሰራተኞችን አታለው በመግባት የያዙዎቸውን ሰነዶች በሙሉ እንደቀሟቸው በደሉ ከተፈጸመባቻ በኋላ ከአቶ ታዲዎስ ታንቱ በስልክ ለመረዳት ተችሏል።

ከልብሶቻቸው በስተቀር ማንኛውንም የጽሁፍ መረጃ ከወሰዱባቸው በኋላ ጠዋት 2.00 ሰዓት ፖሊስ ጣቢያ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥተዎቸው ቢሄዱም ፖሊስ ጣቢያ ሲሄዱ የፖሊስ አዛዡ ስብሰባ አለኝ በሚል ምክንያት ሊያነጋግሩአቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸው ታውቋል። የፖሊስ አዛዡ ከሰአታት ቆይታ በኋላ ለጥቅምት 20/2001 ዓ.ም ተመልሰው እንዲመጡ አቶ ታዲዎስን ቀጥረዋቸዋል።

አቶ ታዲዎስ ታንቱ 1ኛ፣የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መኢአድ በነጻነት ተንቀሳቅሶ እንዲያደራጅ ለክልል መንግስታት፤ ለዞኖችና ለወረዳዎች የጻፈውን ደብዳቤ

2ኛ፣የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፓርቲው የሰጠው የምዝገባ ፈቃድ ሰርቲፊኬት

3ኛ፣መኢአድ ለደቡብ ክልላዊ መንግስት የፃፈው የትብብር ደበዳቤ

4ኛ፣መኢአድ ለሚመለከተው ሁሉ በሚል ያደራጁን የአቶ ታዲዎስ ታንቱን ማንነት የሚገልጽ የትብብር ደብዳቤ ይዘው እየተንቀሳቀሱ ባሉበት ወቅት በመንግስት መዋቅር ከታች ያሉ ክፍሎች እየፈጠሩ ያሉት እንቅፋትና ወከባ ህገ

መንግስቱን የሚጻረር ተግባር መሆኑን ያሳያል ሲሉ የመኢአድ ምክትል ፕሬዚዳንት የደቡብ ቀጠና ሃላፊ ዶክተር ታዬምስ ቦጋለ ገልጠዋል፡፡

ምክትል ፕሬዚዳንቱ እንደገለጹት ፖሊስ የህዝብን ሰላም የመጠበቅ ሃላፊነትና ግዲታ ያለበት መሆኑን በመዘንጋት ሰላማዊ ታጋዮችን ካረፉበት የመኝታ ክፍል ድረስ በውድቅት ሌሊት በመሄድ ሽብር መንዛቱ እጅግ የሚያሳዝን ነው ብለዋል፡፡ አክለውም የፓርቲያችንን ሰነድ በኃይል እየነጠቁ የአባሎቻችንን ስም ዝርዝር በመውሰድ ለማስፈራራትና ለማሸማቀቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ መሆኑን ተገንዝበናል፤ ይህ ደግሞ የበለጠ የሚያጠነክረን እንጂ ወደኋላ የሚያስብለን አለመሆኑን እንቅፋት የሚፈጥሩብን ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል ብለዋል፡፡

በተያያዘ ዜናም የአፋር ክልል የአሳይታ ዞን የመኢአድ ተጠሪና የፓርቲው የላዕላይ ምክር ቤት አበል አቶ አሊሚራህ ያዩ ኢሴ ጥቅምት 17፣ 2001ዓ.ም በአሳይታ ፖሊስ አዛዥ በሻምበል መሃመድ አብደላ ትዕዛዝ እንደታሰሩና ጥቅምት 18፣ 2001 ዓ.ም እንደተፈቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

አቶ አሊሚራህ ያዩ የታሰሩበት ምክንያት የመኢአድን ቢሮ በአሳይታ በመክፈታቸው ገዥው ፓርቲን በማስቆጣቱ ሲሆን፣ ሲፈቷቸውም ለቢሮ የተከራዩትን ቤት በስምንት ቀን ጊዜ ውስጥ እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው፡፡

የግል ቤታቸውን ለመኢአድ ያከራዩት ግለ ሰብ አቶ አሊ ሃረብ በፖሊሶች ግርፋት የደረሰባቸው መሆኑም ታውቋል፡፡

በሰሜን ሸዋ ዞን በአሳግርት ወረዳ የፓርቲው የክልል ተመራጭ የሆኑት አቶ ጌትዬ ደስታ በፖሊሶች ከጥቅምት 15 እስከ 17፣2001 ዓ.ም ድረስ የታሰሩ መሆኑን ከሰሜን ሸዋ ዞን የመኢአድ ተጠሪ ከአቶ ዘውዴ ተፈራ ለመረዳት ተችለሏል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የመኢአድ ላዕላይ ምክር ቤት አባል አቶ በቀለ ግርማ በደቡብ ኢትዮጵያ ጌዲዮ ዞን የማደራጀት ሥራ እያከናወኑ ባሉበት ወቅት በፖሊስ ታስረው በአስከሬ የእስር ቤት አያያዝ ከጥቅምት 2 እስከ 5፣2001 ዓ.ም ድረስ የተንገላቱ መሆናቸው ታውቋል፡፡